# አሲምባ ርዕሰ አንቀጽ

Editor's Note ቁጥር 5/2006 ሐምሌ 26 ቀን 2006 ዓ.ም.

# ታጋይ ይሞታል እንጂ ትግሉስ አይሞትም!

***የወያኔው መንግሥት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ከየመን ጠልፎ በኢቲቪ ማስለፍለፉን እናወግዛለን!***

በሀገራችን ኢትዮጵያ ምድር ለዴሞክራሲያዊ ሕዝባዊ ሥርዓት የሚደረገው መራራ ትግል ከፍተኛ መስዋዕትነትን የሚያስከፍል ለመሆኑ ላለፉት ፶ ዓመታት በእሥር ሥየል እየተፈጸመባቸው ካለፍርድ ለብዙ ዓመታት የተንገላቱ፤ መዳረሻቸው ጠፍቶ ደብዛቸው የሚጠፉትን፣ የተሰደዱትንና ጭካኔ በሞላበት አኳኋን ግድያ የተፈጸመባቸውን ቤት ይቁጠራቸው ከማለት ባሻገር ቆጥረን ይህን ያህል ብለን የምንለካው አይሆንም። ባለፉት ፶ና ዓመታት ከሦሥት ሥርዓቶች ማለትም ከአፄው የባላባት ስርዓት፤ ከደርጉ ምርጥ መኮንኖች ወታደራዊ የፋሺሽቶች ሥርዓትና እነሆ ላለፉት ፳፫ ዓመታት ደግሞ በወያኔ አንጋፋ መሪነት ኢትዮጵያን ከሚጠሉ ጠባብ ብሔረተኞች ጋር እልህ አስጨራሽና አሁንም መስዋዕትነትን የሚያስከፍል ትግል እየተካሄደ ነው። ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተመሥርቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣኑ ባለቤት እስኪሆን ድረስ ትግሉ ይቀጥላል። ትግሉም እስከቀጠለ ድረስ ደግሞ የሚከፈለውም መስዋዕትነት በዚያው መጠን እየጨመረ መሄዱ አይቀርም። የሰሞኑም በአንዳርጋቸው ጽጌ ላይ የደረሰውንም ትግሉ የሚጠይቀን እያንዳንዳችን ልንጎነጨው የማንፈራው የመሥዋዕትነት መራራ ጽዋ መሆኑን ልንገነዘበው ይገባል። ታጋይ ይሞታል እንጂ ትግሉ አይሞትም የሚባለውም ለዚሁ ነው።

ኢትዮጵያውያን ሁሉ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር ቢኖር የአቶ አንዳርጋቸው ከየመን በወያኔና የየመን መንግሥት ሤራ (ሤራው እንኳን ከሁለቱ መንግሥታት በላይ ነው ብለን እናምናለን) የዓለም መንግስታት በሕግ ዕውቅና የሰጡትን መሠረታዊ የሰብዓዊ መብትን የጣሰና ነግ በኔ ብለን በእያንዳንዳችን ላይ እንደተሰነዘረ ልንቆጥረው የሚገባ መሆኑን ነው።  ስለሆነም በአንድ ድምጽ ወጥተን መጮህ የእያንዳንዳችን ፋንታ ነው። አንዳርጋቸው ጽጌ እንደ ግንቦት ሰባት መሪነትም ሆነ በግለ ሰብ ደረጃ ገና ከጅማሮው ኢትዮጵያውያንን የሚያሰባስብ ሚና ከመጫወት ይልቅ ሁሌም ሰልፉ ኢትዮጵያን ከሚጠሉ ከሻቢያ፣ ከኦነጎችና ከመሳሰሉት እንዲሁም ከወያኔም ጋር ጭምር ለዴሞክራሲ የሚደረገው ትግላችን እንዲካፋፈል በየወቅቱ የተጫወታቸውን ሚናዎች የምንረሳው ባይሆንም አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉን መብቱ የተገፈፈን ወገን ይበለው ወይም ድርጅቱ ይጨኽለት የምንለውም ነገር አይሆንም። ለሁሉም የፖለቲካ እሥረኞች መብት ሁላችንም መጮኽ ያቅማማን ጊዜ፣ በኢትዮጵያችን ዴሞክራሲያዊ ሕዝባዊ ሥርዓት እንዲመሠረት እየታገልን ነው የሚለውን አጠያያቂ ያደርገዋል።

የአንዳርጋቸው ጽጌ በየመን መንግሥት ተጠለፈ የሚለው ዜና ከተሰማ ጀምሮ በሀገርቤትም ሆነ በውጭ ያሉትን ኢትዮጵያውያን ሁሉ አሳዝኗል፣ አስቆጭቷል እንጂ ወያኔ እንደፈለገው አላስደነገጠም። በእርግጥ ወያኔን እታገላለሁ የሚለው ወገን ኃይል መከፋፈል አንዱ ችግራችን በመሆኑ፣ ገና አንዳርጋቸው ተጠለፈ የሚለው ዜና እንደተሰማ በምዕራቡ ዓለም የተሰባሰብን ኢትዮጵያውያን በትኩሱ በተደራጀ መልክ በብዛት ወጥተን በየመን ኤምባሲ፣ በተባበሩት መንግሥታት ጽ/ቤት በመሳሰሉት፤ የዓለም አቀፍ ዜና አውታሮች ሊዘሉት በማይችሉት ሁናቴ ብንጮኽ ኖሮ ምናልባትም ሤራውን የምናጋልጥበትና የምናከሽፍበት ዕድላችን ከፍተኛ በሆነ ነበር። በእርግጥ አንዳርጋቸውን አስመልክቶ ብዙ ወገኖች

በየአቅጣጫው የሚያደረጉት እንቅስቃሴ የሚናቅ ባይሆንም በውጭ ካለነው ኢትዮጵያውያን ቁጥር ሲነፃፀር በውቅያኖስ ውስጥ አንዲት የውኃ ጠብታ ያክል በመሆኑ ውጤቱ አመርቂ ይሆናል ብለን ብዙም አንጠብቅም። ስለሆነም ይህንን የሚያበሳጭ ሁናቴ ምክንያት በማድረግ ለሀገራችን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት የሚያታግለን ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ኃይል ለመገንባት ያስቸገረን ምንድር ነው? ምንስ መደረግ አለበት? ለሚለው መልስ ማግኘት የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ ነው እንላለን።

በመጀመሪያ እኛ ኢትዮጵያውያን በሀገራችን የምንፈልገውን ዴሞክራሲያዊ ሕዝባዊ ሥርዓት በትግል ማምጣት የምንችለው እኛው ኢትዮጵያውያን በምንከፍለው መስዋዕትነት ብቻ መሆኑን ልንተማመን ያስፈልጋል። ሀገር በቀሎችም ሆነ የውጪ ኢትዮጵያን የሚጠሉ ኃይሎች በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሕዝባዊ ሥርዓት እንዳይመሠረት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚጫወቱትን ሚና ደግሞ ማጤን ሌላው ግንዛቤአችን ሊሆን ይገባዋል። ለትግላችን ትልቁ ማጥቂያ መሣሪያችን ደግሞ በተለያዩ ድርጅቶችም ውስጥ ቢሆን <u>በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር</u> በመሰባሰብ በመካከላችን ያለውን መተማመን በጥንቃቄ በመገንባት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ በማንኛውም ዓይነት መንገድ <u>መደራጀት መደራጀት መደራጀት</u> ነው። ውጤት ሊያመጣ የሚችል ጠንካራ የመታገያ ድርጅትን መፍጠርና በግብታዊነትና በስሜታዊነት ብቅ ብለው እንደ ማለዳ ጤዛ ብትን የሚሉትን ስብስቦች አበራይቶ መለየት አስፈላጊ ነው። ሽልምልም ያለ ድረ-ገጽ፣ ሶሻል ሚዲያ፣ ቃጭሉ የበዛ ራዲዮ ወይም የሳተላይት ቴሌቪዥንና የመሳሰሉት አታጋይ ድርጅትን አይተኩም።

ለምሳሌ ሰሞኑን አንዳርጋቸው ጽጌ ተጠለፈ የሚል ዜና በውጪው ዓለም ላለነው እንደተሰማ፣ ከላይ እንዳስቀመጥነው በውጭ ያለን ኢትዮጵያውያን የወያኔ ሥርዓት ያንገሸገሸንን ያክልና እንደብዛታችን በዓለም መድረኮች በብዛት በመውጣት ድምፃችን ከፍ ብሎ አለመሰማቱ የኢትዮጵያውያን መከፋፈል ዋናው ሕመማችን መሆኑን ተገንዝበን ለዚሁ መፍትሄ ለመፈለግ ጥረት ከመድረግ ይልቅ በሚያሳዝን ሁናቴ በየፊናችን በስሜት እየጋለብን መገኘታችን ነው። ጠንካራ ድርጅትን መሠረት ያላደረገ ባዶ መፈክር፣ ለምሳሌ <u>“እኔም አንዳርጋቸው ነኝ”</u> ብሎ በተናጠል በየ ድረ-ገጹና ሶሻል ሚዲያውም ሆነ በየሳተላይት ቴሌቪዥኑ አንዱ ከሌላው በላይ ለመጮኽ መሽቀዳደሙ በስሜት ያዙን ልቀቁን እንዳይሆን እንፈራለን። በሻቢያ በኩል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት ይገኛል ብለን ባናምንም <u>“እኔም አንዳርጋቸው ነኝ”</u> ብሎ ያንዳርጋቸውን ምስልና መፈክሩን በቲ-ሸርት የለበሰ ሁሉ ወደ አሥመራ ሊሄድ ይነሳል ብለን ከቶውንም አንጠብቅም። ስለገንዘብ ማሰባሰቡም ሆነ በየመባቻው የምንከምረው ሳይገሉ ጎፈሬ የአርበኞች ጋጋታም ሆነ ባለፉት ፳፫ ዓመታት ለዴሞክራሲው ትግል ተብሎ የተሰበሰበውን ገንዘብ ብንለካውና በየምክንያቱ ጣጥለውን የሸሹትን ወይም ትግሉን የሸጡትን ማንዴላዎቻችን ለአንድ አፍታ ብናስባቸው በትንሹ ሦሥት የወያኔ ሥርዓቶችን የምንጥልበት ኃይል በሆኑልን ነበር ብንል ማጋነን አይሆንም። እዚህ ላይ ወገኖች በአሁኑ ወቅት በየፊናቸው እያደረጉ ያሉትን እንቅስቃሴ ለማንኳሰስ ሳይሆን ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በመካከላችን ላለፉት ፳፫ ዓመታት በተለያዩ ተዋንያን የተገነባብንን ያለመተማመን ግንብ አፍርሰን በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ሀ ብለን ዕምነታችንን በጥንቃቄ ገንብተን ሚዛን የሚደፋ ኃይል ሆነን መውጣት

ካልቻልን በስሜት ብቻ ሆ! እያልን በየአቅጣጫው ብንጋልብ የትግላችን ውጤት አመርቂ መሆን አለመቻሉን ለመጠቆም ያክል ነው።

ለማጠቃለል፦

እንደ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ግንቦት ሰባት በሻቢያ ጥላ ሥር ኢትዮጵያን ነፃ የሚያወጣ ጦር አዘጋጅቻለሁ ብሎ ካወጀ ጀምሮና (ለብዙዎቻችን ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ አይነት ነገር ነው) በተለይም ደግሞ ድርጅቱ እንደ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ከኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ግንኙነቱን አጠንክሮ ወያኔን ሊፈታተን የሚችል አንደኛው ተጨማሪ ኃይል ሆኖ ከመውጣት ይልቅ የድርጅቱ ጊዜ ጉልበትና ንብረት በአልባሌና በሚያሳዝን ሁናቴ ኢትዮጵያዊውን ኃይል የሚያዳክም ስልት በመከተል ኢትዮጵያን ከሚጠሉ ክፍሎች ማለትም የሻቢያ፣ የኦነግ ብልጣብልጦች የመሳሰሉትና ትላንትና የሕዝብ ልጆችን ካረዱ የደርግ ኢሰፓዎች፣ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ጨምሮ በኢሳት ቴሌቭዥኑ ተከላካይ መድረክ ሆኖ መገኘቱ አሳዝኖን በየጊዜው ለምናሰማው ተቃውሞም ሆነ ነቀፌት ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ባለው የሚዲያ ኃይልም ሆነ የገንዘብ ድጋፍ የልብ ልብ ተሰምቶት በማን አለብኝነት የተንገዋለለ ድርጅት ነው ብለን ብናምንምና፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ አንዳርጋቸው ጽጌ ወያኔ ወደ ሥልጣን ከመውጣቱ በፊትና በኋላም አብሮአቸው በባለሥልጣንነት አጅቦ የነበረ፤ በቅንጅት ጊዜ በስደት ከመካከላችን እስኪቀላቀል ድረስ ማለት ነው፤ ከዚያም ግንቦት ሰባት ከመፈጠሩ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ ከጥቂት ሳምንታት በፊት በወያኔ እጅ እስከ ወደቀባት ጊዜ ድረስ ፀረ-ወያኔው ታጋይ ኃይል ተካፋፍሎ ዳካማ እንዲሆን ካስቻሉት ህመሞቻችን አንዱ ሆኖ እንደ ግለሰብ የተጫወታቸውን ሚናዎች ባንረሳም፤ ወያኔ በየመንና በሌሎች ኃይሎች <u>አማካይኝነት የሰብዓዊ መብቱን መገፈፉን አጥብቀን እንቃወማለን! ወያኔንና የየመንን መንግሥታ እናወግዛለን!</u> ኢትዮጵያዊ ኃይሎች ይህንን ወቅት በመጠቀም በስሜት በያቅጣጫው ከመነዳታችን በፊት ጥንቃቄ የተሞላበት መሰባሰብ ልናደርግ የምንችልበትን ሁናቴ ማመቻቸቱ ተገቢ ነው እንላለን። ለዚህ ደግሞ የምንወጃጀልበት ሳይሆን በመሠረታዊ ችግሮቻችንን በቅንነት በግልጽ ተወያይተን የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ የትግል ዕቅድ የምንነድፍበት ሀገራዊ መድረክ መመሥረቱ ተገቢ ነው እንላለን።

የአሲምባ ድረ-ገጽ ዝግጅት ክፍል

ኢትዮጵያዊው ኃይል ተደራጅ! ተደራጅ! ተደራጅ!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል